## ሕግን የማስከበር እርምጃ ሕግን የተከተለ መሆን አለበት

## በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በሚገኙ 21 ፖሊስ ጣቢያዎች ላይ የተደረገ የክትትል ሪፖርት

### ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) ከህዳር 11 ቀን 2013 ዓ.ም. እስከ ጥር 04 ቀን 2013 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ያለውን የእስረኞችን ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ በተመለከተ በተለይም የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በቁጥጥር የዋሉ ተጠርጣሪዎችን ጨምሮ ሌሎችም "በወቅታዊ ሁኔታ" ("haala yeroo")[1] የተያዙ የሚባሉ ብዛት ያላቸው እስረኞች ከሚገኙባቸውና ተደጋጋሚ ቅሬታዎች ከሚቀርቡባቸው መካከል በ21 የተመረጡ ፖሊስ ጣቢያዎች ላይ ክትትል አድርጓል፡፡

በተደረገው ክትትል ከቦታ ቦታ መጠኑ ቢለያይም የእስረኞችን አያያዝ በተመለከተ በርካታ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች መፈጸማቸውን የሚያመላክቱ መረጃዎች ቀርበዋል፡፡ ብዙ ሰዎች ያለ ፍርድ ቤት የመያዣ ትዕዛዝ "በወቅታዊ ሁኔታ" የተጠረጠሩ ናቸው በሚል ይታሰራሉ፣ ከነዚህም አብዛኞዎቹ ምርመራ ሳይጀመርባቸው እና ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ በሕግ ከተቀመጠው ጊዜ በላይ ታስረው ይቆያሉ፡፡ በተጨማሪም በብዙ ፖሊስ ጣቢያዎች ዐቃቤ ሕግ በቂ መረጃ ባለመገኘቱ ምክንያት "የአያስከስስም ውሳኔ" የሰጠባቸው ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት መለቀቅ የነበረባቸው ተጠርጣሪዎች ዋና ተሳታፊ (ኮር) ናቸው ወይም በሌላ ወንጀል ይፈለጋሉ በሚል ያለ አግባብ ታስረው እንዲቆዩ የተደረጉ ሰዎች ነበሩ፡፡ የተለያዩ ፖሊስ ጣቢያዎች ኃላፊዎች "በወቅታዊ ሁኔታ" ተጠርጥረው የታሰሩ እስረኞች ጉዳያቸው የሚታየው በዞን እና በወረዳ ደረጃ በተቋቋሙ "የፀጥታ ምክር ቤቶች" (Mana maree nageenyaa)[2] መሆኑን

[1] "በወቅታዊ ሁኔታ" (Haala yeroo) የተያዙ የሚባሉ ተጠርጣሪዎችን በተመለከተ በንዑስ ክፍል 3.1. የቀረበውን አጭር ማብራርያ ይመልከቱ፡፡

[2] የምክር ቤቱ አደረጃጀት እና አሰራር ላይ የቀረበ ማብራርያ በንዑስ ክፍል 3.5 ስር ይመልከቱ፡፡

ይገልጻሉ። የፍርድ ቤቶች ትእዛዝ አለመከበር በክልሉ አንዳንድ ቦታዎች አሁንም የቀጠለ ችግር ነው።

ክትትል በተደረገባቸው የፖሊስ ጣቢያዎች ከሚገኙት እስረኞች መካከል የተወሰኑት በፖሊሶች በሚያዙበት ወቅት (በተለይም በኦሮሚያ ልዩ ሀይል) እንዲሁም በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ድብደባ የተፈጸመባቸው መሆኑን ለክትትል ቡድኑ የገለጹ ሲሆን በዚሁ ምክንያት ጭንቅላታቸው፣ ፊታቸው፣ አፍንጫቸው፣ ሆዳቸው፣ እግራቸው፣ ጥርሳቸው ወ.ዘ.ተ. ላይ ጉዳት ደርሶባቸው ገና ያልዳነ ቁስል፣ ስብራት ወይም ደም በሰውነታቸው ላይ የሚታይ እና ለጊዜያዊ እና ቋሚ የአካል ጉዳት የተዳረጉ እስረኞች መኖራቸውን የኢሰመኮ የክትትል ቡድን ተመልክቷል። በተወሰኑ ቦታዎች "የኦነግ ሸኔ" አባል ወይም ደጋፊ ናቸው በሚል የሚፈለጉ "ልጆቻችሁን አቅርቡ" በማለት አባት ወይም እናትን ማሰር፤ "ባልሽን አቅርቢ" በማለት ሚስትን ማሰር እንዲሁም ሰዎችን ያለ አግባብ በማሰር "የኦነግ ሸኔ" አባል ናችሁ ብለን እንከሳችኋለን በማለት በማስፈራራት ገንዘብ የመጠየቅ ሁኔታዎች መኖራቸውን የተለያዩ እስረኞች ቅሬታዎችን አቅርበዋል። በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች ደግሞ ከጥቃቅን እና አነስተኛ የብድር ተቋማት የተበደሩትን ገንዘብ ባለመመለሳቸው ወይም ገንዘቡን ተበድረው ላልመለሱ ሰዎች ዋስ በመሆናቸው ጋር በተያያዘ የፍትሐ ብሔር ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው በእስር ላይ የነበሩ ሰዎችን የክትትል ቡድኑ ተመልክቷል።

ክትትሉ በተደረገባቸው በሁሉም ፖሊስ ጣቢያዎች ሴት እስረኞች ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል ራሳቸው በወንጀል ተጠርጥረው የታሰሩ ወይም ሌላ በወንጀል የሚፈለግ የተሰወረ የቤተሰብ አባል አቅርቡ ተብለው የታሰሩ መሆናቸውን የሚገልጹ ሴቶች ነበሩ። ከእነዚህ ሴቶች መካከል የተወሰኑት እድሜያቸው ከ 5 ወር እስከ 10 ዓመት የሚሆናቸው ሕጻናት ልጆቻቸውን ይዘው የታሰሩ ናቸው። በሌላ በኩል በተለያዩ ፖሊስ ጣቢያዎች በወንጀል ነክ ጉዳዮች ተሳታፊ ናቸው በሚል ተጠርጥረው የታሰሩ እድሜያቸው ከ 9 እስከ 18 ዓመት የሚሆናቸው ሕጻናት አካለ መጠን ከደረሱ ሰዎች ጋር ተቀላቅለው በእስር ላይ እንደሚገኙ ኮሚሽኑ ተመልክቷል።

የኢሰመኮ የክትትል ቡድን በተመለከታቸው በአብዛኛዎቹ ፖሊስ ጣቢያዎች ያሉት የማረፍያ ክፍሎች በእስረኞች የተጣበቡ ናቸው። የተወሰኑ እስር ቤቶች ውስጥ የከፋ የእስረኛ መጨናነቅ በመኖሩ ምክንያት በቀን ውጪ በረንዳ ላይ በመዋል በማታ ደግሞ በተራ የሚተኙበት ሁኔታ መኖሩን ጭምር እስረኞች ለክትትል ቡድኑ ገልጸዋል። አብዛኛዎቹ የማረፍያ ክፍሎች ከፍተኛ የንጽህና ጉድለት ያለባቸው እና ለተባይ የተጋለጡ መሆናቸውን የክትትል ቡድኑ

ተመልክቷል። ከዚህም በተጨማሪ ከፍተኛ የምግብ እጥረት መኖሩንና በዚህም ምክንያት በተለይ ከመደበኛ መኖርያቸው ርቀው በመታሰራቸውና በአቅም ማነስ ምክንያት ከቤተሰቦቻቸው ምግብ የማይቀርብላቸው እስረኞች ለከፍተኛ ችግር የተዳረጉ መሆኑን እንዲሁም የውሃ፣ የመጸዳጃ እና የሕክምና አገልግሎት አቅርቦት ችግር መኖሩን ለመረዳት ተችሏል።

የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የኮሚሽኑን ግኝቶች በተመለከተ ከኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ጋር የምርመራ ቡድን በማዋቀር የማጣራት ሥራ መሥራቱን በመጥቀስ ዝርዝር መልስ ሰጥቷል። በምላሹም የተጠቀሱት የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳልተፈጸሙና የኮሚሽኑ ግኝቶች "አብዛኛዎቹ ከእስረኞችና ከቤተሰቦቻቸው የተወሰዱ የአንድ ወገን መረጃዎች" ናቸው በሚል ያስተባበለ ሲሆን አንዳንድ ችግሮች የተከሰቱት የሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ "የነበረውን ከፍተኛ የጸጥታ ችግር ለመፍታት … በተለመደው መንገድ የሕግ የበላይነትን ለማስከበር የማይቻል" በመሆኑ እንደሆነ ይገልጻል። ኢሰመኮ የቀረቡት ግኝቶች ከእስረኞች እና ከቤተሰቦቻቸው ከተገኙት መረጃዎች በተጨማሪ የተወሰኑት በክትትል ቡድኑ አካላዊ ምልከታ እና በአንዳንድ የፖሊስ ጣቢያዎች ተወካዮች ጭምር የተረጋገጡ መሆናቸውን ያስገነዝባል። በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተሰጠውን ዝርዝር ምላሽ በተመለከተ ምላሾቹ በዚህ የክትትል ሪፖርት በተገቢው ቦታ እንዲካተቱ ተደገርገዋል፤ እንዲሁም የምላሹ ደብዳቤ በአባሪነት ተያይዟል።

**ምክረ ሃሳቦች**

ኢሰመኮ በዚህ ሪፖርት የተመለከተው የተወሰኑ ቦታዎችን ቢሆንም፤ ተመሳሳይ የሰብአዊ መብቶች ችግሮች በብዙ የክልሉ አከባቢዎች የሚስተዋሉ መሆኑን በተለያዩ ጊዜያት ለኮሚሽኑ ሲቀርቡ ከነበሩ አቤቱታዎች መረዳት ይቻላል። በመሆኑም ሁሉም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የችግሮቹን አሳሳቢነት በመረዳት ከታች የተዘረዘሩትን ምክረ ሃሳቦች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ኢሰመኮ ጥሪ ያቀርባል።

**ለኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን እና ለኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ**

- የፍርድ ቤት ውሳኔን በመጻረር በእስር ላይ እንዲቆዩ የተደረጉ እስረኞች በሙሉ በአስቸኳይ እንዲፈቱ፤

- ☞ በፀጥታ ኃይሎች ድብደባ እና ሌሎችም ኢሰብአዊ ድርጊቶች የተፈጸመባቸው እስረኞችን ጉዳይ በማጣራት ተጎጂዎች ፍትሕ እንዲያገኙ እና የሙያ ሥነምግባር ጉድለትና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን የፈጸሙ የፖሊስ አባላት ተጠያቂ እንዲሆኑ እንዲደረግ እና ለወደፊትም ተመመሳሳይ ድርጊቶች እንዳይደገሙ አስፈላጊ የሆነው የቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጋ፤
- ☞ የተጠረጠሩበት ወንጀል ሳይነገራቸው፣ ምርመራ ሳይደረግባቸው እና ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ለረጅም ጊዜ በእስር ላይ የሚገኙ "በወቅታዊ ሁኔታ" የታሰሩ የሚባሉ ተጠርጣሪዎች ምርመራቸው እንዲፋጠን እና ፍርድ ቤት ቀርበው ፍትሃዊ ውሳኔ እንዲሰጣቸው እንዲደረግ፣ በወንጀል ሊያስከስሳቸው የሚያስችል ማስረጃ ያልተገኘባቸው ተጠርጣሪዎች እንዲለቀቁ፤
- ☞ በወንጀል የሚፈለግ የቤተሰብ አባል አቅርቡ ተብለው በእስር ላይ ያሉ ሰዎች በስቸኳይ እንዲፈቱ፤ እንዲሁም ወደፊትም ተመሳሳይ ድርጊቶች እንዳይደገሙ ግልጽ የሆነ አመራር እንዲሰጥ፤
- ☞ ከፍተኛ የእስረኛ መጨናነቅ ባለባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች የእስረኞችን ቁጥር ለመቀነስ የሚረዱ አፋጣኝ እርምጃዎች እንዲወሰዱ፤ እንዲሁም ተጨማሪ የማረፍያ ክፍሎች እንዲገነቡ፣ የንጽህና ሁኔታን ለማሻሻል አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ፣
- ☞ የፍትሐ ብሔር ግዴታዎችን ካለመወጣት ጋር በተያያዘ የታሰሩ ሰዎች በአስቸኳይ ከእስር እንዲፈቱ እና ለወደፊትም ተመሳሳይ ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ ግልጽ የሆነ አመራር እንዲሰጥ፣
- ☞ በማንኛውም ጊዜ ለሕጻናት እና ሴቶች ተጠርጣሪዎች ቅድሚያ ተሰጥቶ የተጠረጠሩበት ወንጀል በአፋጣኝ ምርመራ እንዲደረግ፤
- ☞ የሕጻናት ልጆች እናቶች በተቻለ መጠን በዋስ ተለቀው ጉዳያቸውን ከውጪ ሆነው መከታተል የሚችሉበት ሁኔታ እንዲመቻች፤
- ☞ በወንጀል ነክ ጉዳዮች ተሳታፊ ናቸው በሚል ተጠርጥረው የታሰሩ እድሜያቸው ከ 9 እስከ 15 ዓመት የሚሆናቸው ሕጻናት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 172 መሰረት በአፋጣኝ በዋስ እንዲለቀቁ።

### ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳደር

- ☞ በዞን እና በወረዳ ደረጃ የተቋቋሙ "የፀጥታ ምክር ቤቶች" የፍትሕ አካላትን ስልጣን እና ተግባር ባከበረ መልኩ እንዲሰሩ እንዲደረግና ከሰዎች መታሰርና ከእስር መለቀቅ ጋር በተያያዘ የሚያከናውኑትን ተግባሮች እንዲያቆሙ፤

☞ በተለያዩ ቦታዎች የሥራ ስምሪት የሚሰጣቸው የፀጥታ ሀይሎች ተገቢ የሆነ ቁጥጥር እንዲደረግባቸው፡፡

**ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለጨፌ ኦሮሚያ**

☞ በዚህ ሪፖርት የተገለጹ አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኙ የኮሚሽኑ ምክረ ሀሳቦች እየተፈጸሙ መሆኑን በቅርበት ክትትል እና ቁጥጥር እንዲደረግ፤ ኢሰመኮ ጥሪ ያደርጋል፡፡

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ምሽት የተፈጸመውን የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል የተፈጠረው አለመረጋጋት ያስከተለውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በተለይም የእስረኞች አያያዝን በሚመለከት በተለያዩ ጊዜያት ክትትል በማድረግ በተለዩ ክፍተቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለሚመለከታቸው አካላት ምክረ ሃሳቦችን ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡

በተሰጡት ምክረ ሃሳቦች መሠረት የተወሰኑ የማስተካከያ እርምጃዎች ቢወሰዱም በክልሉ አሁንም ድረስ በርካታ ያልተፈቱ የሰብአዊ መብቶች ችግሮች መኖራቸውን የሚያመለክቱ አቤቱታዎች ለኢሰመኮ ይቀርባሉ፡፡ ኢሰመኮ ከህዳር 11 ቀን 2013 እስከ ጥር 04 ቀን 2013 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በተለይ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በቁጥጥር የዋሉ ተጠርጣሪዎችን ጨምሮ ሌሎችም "በወቅታዊ ሁኔታ" ("haala yeroo") የተያዙ የሚባሉ ብዛት ያላቸው እስረኞች ከሚገኙባቸውና ተደጋጋሚ ቅሬታዎች ከሚቀርቡባቸው መካከል በ21 የተመረጡ ፖሊስ ጣቢያዎች የክትትል ሥራ አከናውኗል፡፡

ክትትሉ የተደረገው በጅልዱ፣ አቡነ ግንደበረት፣ ግንደበረት፣ ባቱ፣ አዳሚ ቱሉ፣ ሻሸመኔ ከተማ (ወረዳ ሁለት ፖሊስ ጣቢያ)፣ አርሲ ነጌሌ ከተማ፣ ዶዶላ፣ አዳባ፣ ገደብ አሳሳ ወረዳ (አሳሳ)፣ አዳማ (በደንበላ ክፍለ ከተማ፣ ዳቤ ሶሎቄ ክፍለ ከተማ እና ቦሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ጣቢያዎች)፣ አሰላ ከተማ (ሁለት ፖሊስ ጣቢያዎች)፣ ዴራ (ዶዶታ ወረዳ)፣ ጭሮ፣ ቦሰት ወረዳ (ኦለንጪቲ)፣ ሮቤ ባሌ ከተማ፣ ሀሮማያ እና አወዳይ በሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች ላይ ነው፡፡

## 2. የክትትሉ ዘዴ

ክትትሉ የተደረገው ለኮሚሽኑ የቀረቡ ተደጋጋሚ ቅሬታዎችን እና ጥቆማዎችን መሠረት በማድረግ በተለይም የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በቁጥጥር የዋሉ ተጠርጣሪዎችን ጨምሮ ሌሎችም "በወቅታዊ ሁኔታ" የተያዙ የሚባሉ ብዛት ያላቸው እስረኞች በሚገኙባቸው በ 21 የተመረጡ ፖሊስ ጣቢያዎች ላይ ነው። የክትትል ሥራው እያንዳንዳቸው ሁለት አባላት ያሉት ሁለት ቡድኖችን በሁለት ዙር በፖሊስ ጣቢያዎቹ በማሰማራት የተከናወነ ሲሆን ሁለቱም ቡድኖች የእስረኞችን ሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ በተመለከተ ተገቢነት ያላቸውን ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ሕጎችን እና መርሆችን መሠረት በማድረግ ቀደም ብሎ የተዘጋጁ መጠይቆችን በመጠቀም ከተመረጡት 21 ፖሊስ ጣቢያዎች ኃላፊዎች ወይም ተወካዮች እና በእነዚህ ፖሊስ ጣቢያዎች የሚገኙ 281 እስረኞችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ እንዲሁም በማረፊያ ክፍሎች በመገኘት አካላዊ ምልከታ በማድረግ መረጃዎችን አሰባስበዋል።

ይሁንና በዚህ ሪፖርት ሁኔታውን ለመግለጽ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት ከተጠቀሱት የቦታ ስሞች እና ክስተቶች በስተቀር የግለሰቦችን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የክትትል ቡድኖቹ ያነጋገሩዋቸው እስረኞች እና የፖሊስ ጣቢያዎቹ ተወካዮች ስሞቻቸው አልተጠቀሱም።

ኮሚሽኑ የክትትል ሥራውን ግኝቶች ለሕዝብ ይፋ ከማድረጉ በፊት በክትትሉ በተለዩ ዋና ዋና የእስረኞች ሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኦሮሚያ ክልል መስሪያ ቤቶች (ጨፌ ኦሮሚያ፣ የኦሮሚያ ብ/ክ/መ ፖሊስ ኮሚሽን፣ የኦሮሚያ ብ/ክ/መ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ እና የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት) አስተያየት እንዲሰጡበት ጥር 14 ቀን 2013 ዓ.ም. በተላከ ደብዳቤ (ቁጥር ሰመኮ/2.1/50/2013) ጠይቋል። ጨፌ ኦሮሚያ እና የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ባለመስጠታቸው አስተያየታቸውን ማካተት አልተቻለም። የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መጋቢት 14 ቀን 2013 ዓ.ም. በቁጥር 02/WG-12/1172 ለኢሰመኮ በጻፈው ደብዳቤ የኮሚሽኑን ግኝቶች በተመለከተ ከኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ጋር የምርመራ ቡድን በማዋቀር የማጣራት ሥራ መሥራቱን በመጥቀስ ዝርዝር መልስ የሰጠ ሲሆን ምላሾቹ በዚህ ሪፖርት በተገቢው ቦታ እንዲካተቱ ተደገርገዋል።

## 3. በክትትሉ የተለዩ ዋና ዋና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች

በክልሉ በእስረኞች አያያዝ ረገድ የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ ተጎጂዎች ፍትሕ እንዲያገኙ እና የመብት ጥሰት ፈጻሚዎች ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማረጋገጥ ኮሚሽኑ በቀጣይነት የሚያደርጋቸው የክትትልና የምርመራ ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆነው በአብዛኞቹ ክትትል በተደረገባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች ያለው የእስረኞች አያያዝ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ የተወሰኑ ማሳያዎችን ብቻ በመጥቀስ በክትትሉ የተለዩ ዋና ዋና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 3.1. አላግባብ እስር እና ተያያዥ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች

የክትትል ቡድኑ በፖሊስ ጣቢያ ከሚገኙ ተጠርጣሪዎች እና ከፖሊስ ጣቢያ አመራሮች ጋር ባደረጋቸው ውይይቶች በአብዛኞቹ ክትትል በተደረገባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች የነበሩ እስረኞች “በወቅታዊ ሁኔታ” (“haala yeroo”) ተጠርጥረው የታሰሩ መሆናቸውን ለመረዳት ችሏል። ይህ ሀረግ በአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያ ማግስት ከተፈጠረው የሰላም መደፍረስ ጋር በተያያዘ የታሰሩ ሰዎችን፣ በተለያዩ ጊዜያት ሲጠሩ ከነበሩ የአድማና የተቃውሞ ሰልፎች ጋር በተያየዘ የታሰሩ እስረኞችን፣ “የኦነግ ሸኔ” አባል ወይም ደጋፊ ተብለው የታሰሩ ሰዎችን፣ በትግራይ ክልል ከተፈጠረው ሁኔታ ጋር በተያያዘ የታሰሩ የትግራይ ተወላጆችን እና በመሰል ከፖለቲካ ጋር ተያያዥነት ባላቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍ ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ተጠርጥረው የታሰሩ ሰዎችን ለመግለጽ የሚጠቀሙበት መሆኑን የፖሊስ ጣቢያዎቹ ኃላፊዎች ያስረዳሉ።

የፖሊስ ጣቢያ ኃላፊዎች “በወቅታዊ ሁኔታ” ተጠርጥረው የታሰሩ እስረኞች ጉዳያቸው የሚታየው በዞን እና በወረዳ ደረጃ በተቋቋሙ “የፀጥታ ምክር ቤቶች” (Mana maree nageenyaa) መሆኑን ይገልጻሉ። የምክር ቤቱ ውሳኔ አሰጣጥ የተንተተ እና የሚሰጣቸው ውሳኔዎችም ሕግን ያላከበሩ እንደሆኑ እስረኞች ይናገራሉ። በዚሁ ምክንያት በብዙ ፖሊስ ጣቢያዎች የተጠረጠሩበት ወንጀል በአግባቡ ሳይነገራቸው፣ ምርመራ ሳይጀመርባቸው፣ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ፣ ክስ ሳይመሰረትባቸው፣ የዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ባለመከበሩ እና የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ባለማክበር ጭምር ያለ አግባብ በእስር የቆዩ መሆኑን በመግለጽ እስረኞች ቅሬታቸውን ያቀርባሉ።

በአንዳንድ አከባቢዎች (ለምሳሌ አዳባ፣ አሳሳ) እስሩ የሚከናወነው በዘመቻ (operation) መልክ ሌሊት ጭምር መሆኑንና የቤታቸው በር እየተሰበረ የፍርድ ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ባልያዙ ልዩ ሀይሎች እና መደበኛ ፖሊሶች ከቤታቸው ተወስደው የታሰሩ መሆኑን ለክትትል ቡድኑ የገለጹ እስረኞች ነበሩ፡፡

ባለጉዳዮቹ ለኢሰመኮ እንደገለጹትና የፖሊስ ኃላፊዎችም እንዳረጋገጡት፤ በአዳማ ከተማ አንዲት እርጉዝ ሴትን ጨምሮ ከአንድ ካፌ ውስጥ "አድማ ለመጥራት ሲወያዩ ነበር" ተብለው የተያዙ 38 ተጠርጣሪዎች የጊዜ ቀጠሮ መዝገባቸው የተዘጋ እና ፍርድ ቤት የዋስትና መብት የፈቀደላቸው ቢሆንም መጀመሪያ የያዛቸው ፖሊስ "በሥራ ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ በመዛወሩ ምክንያት ቀርቦ የምስክር ቃል መስጠት ባለመቻሉ" እና "ያሉት ሌሎች ማስረጃዎች ደግሞ ተጠርጣሪዎቹን ለመክሰስ በቂ አይደሉም" በሚል ምክንያት ከአራት ወራት በላይ በእስር እንዲቆዩ ተደርገዋል፡፡

በአርሲ ነጌሌ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ የአርቲስት ሃጫሉ ግድያን ተከትሎ ከተፈጠረው የሰላም መደፍረስ ጋር በተያያዘ በወንጀል ድርጊቶች ተሳትፈዋል በሚል ተጠርጥረው የተያዙና የምርመራ መዝገባቸው በፍርድ ቤት የተዘጋ እና ክስ ያልተመሰረተባቸው 16 ተጠርጣሪዎች "ባይከሰሱም ዋና ተሳታፊዎች በመሆናቸው፤ ስልጠና መግባት አለባቸው" በሚል ከአራት ወራት በላይ በእስር እንዲቆዩ ተደርገዋል፡፡ ከነዚህ መሃከል አንዲት እስረኛ "በሌሎች ተከሳሾች ላይ ካልመሰከርሽ" ተብላ ፍቀደኛ ሳትሆን በመቅረቷ ታስራ እንድትቆይ መደረጓን እና በፖሊሶች እና በዐቃቤ ሕግ ማስፈራሪያ የደረሰባት መሆኑን ተናግራለች፡፡ የፖሊስ ጣቢያው አስተዳደርም እስረኞቹ ኮር (ዋና ተሳታፊዎች) ተብለው የተለዩ በመሆናቸው ወደ ማሰልጠኛ ካምፕ እንዲገቡ በበላይ አካል የተወሰነ መሆኑን በመግለጽ ነገር ግን ከሌሎች ቦታዎችም ስልጠና የሚገቡ እስረኞች በመኖራቸው ሂደቱ የተጓተተ መሆኑን ጠቅሶ በተከሳሾች ላይ አልመሰክርም በማለቷ በእስር ላይ የነበረችን ተከሳሽ በሚመለከት ግን "ማስረጃ ስላለን በዋና ተሳታፊነት እንከሳታለን" የሚል አስተያየት ሰጥቷል፡፡

በባቱ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ከነበሩ እስረኞች መካከል 10 ተጠርጣሪዎች እንዲሁም በአዳሚ ቱሉ በፖሊስ ጣቢያ ተይዘው ከነበሩ ተጠርጣሪዎች መካከል 22 ሰዎች ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ያለ አግባብ ከአንድ ወር እስከ አምስት ወር ታስረው እንዲቆዩ መደረጋቸውን ለክትትል ቡድኑ ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ በጭሮ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ከተለያዩ ወረዳዎች ተይዘው በጣቢያው በአደራ መልክ እንዲቆዩ የሚደረጉ ተጠርጣሪዎችን ጨምሮ ሌሎችም እስረኞች ፍርድ ቤት

ሳይቀርቡ ለወራት ታስረው እንዲቆዩ መደረጋቸውን በመጥቀስ ለክትትል ቡድኑ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

በአዳባ ከአሥራ አምስት ቀናት እስከ ሁለት ወራት ለሚደርስ ጊዜ የታሰሩ 30 ሰዎች፤ በዱራ ከአንድ ወር ከግማሽ በላይ የታሰረ አንድ ሰው እንዲሁም በአሰላ ወረዳ 1 እና አሰላ ወረዳ 2 ከአሥራ አምስት ቀናት እስከ ሦስት ወራት ድረስ የታሰሩ አራት ሰዎች ክስ ሳይመሰረትባቸው በእስር የሚገኙ መሆኑን የኢሰመኮ የክትትል ቡድን ተመልክቷል፡፡ ሕጋዊ ሂደትን ያልተከተለ እስር መኖሩን የኢሰመኮ የክትትል ቡድን በተለያዩ ፖሊስ ጣቢያዎች ካደረገው ምልከታ የተረዳ ሲሆን በወቅቱ ያነጋገራቸው እስረኞችም በተጨናነቁ የማረፍያ ክፍሎች ውስጥ፣ በቂ ምግብ በማያገኙበት ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ያለ አግባብ ታስረው እንዲቆዩ መደረጋቸውን ይገልጻሉ፡፡

በአዳባ ፖሊስ ጣቢያ የክትትል ቡድኑ ያነጋገራቸው አንድ እድሜያቸው በግምት ከሃምሳ ዓመት በላይ የሆነ ሰው፤በወረዳው እሳቸው እና ሌሎች ብዙ ሰዎች ከሁለት ወር በላይ ያለ ምንም የሕግ ሂደት በእስረኛ በተጣበቡ ክፍሎች ውስጥ ያለ ምንም መከላከያ ቁሳቁስ ለኮቪድ-19 በሽታ አጋላጭ በሆነ ሁኔታ ለወራት መታሰራቸውን፣ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ እየተከበረ አለመሆኑን እና በእስረኞች ላይ በልዩ ሀይሎች ድብደባ የሚፈጸም መሆኑን በማስመልከት "ከዚህ በፊት በነበሩ ጊዜያት በፖለቲካ ምክንያት በተደጋጋሚ ታስሬ አውቃለሁ፣ ነገር ግን በህይወት ዘመኔ እንዲህ አይነት ሁኔታ አላየሁም" በማለት ቅሬታቸውን ለክትትል ቡድኑ አስረድተዋል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ክትትል በተደረገባቸው አካባቢዎች ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰዎች በብዛት መታሰራቸውን እና ለተራዘመ ጊዜ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ በእስር እንዲቆዩ መደረጋቸውን በማስመልከት በቀረበው ቅሬታ በላይ በሰጠው ምላሽ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በነበረው የሰላም መደፍረስ በተፈጠረው ውስብስብ ሁኔታ ምክንያት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በቁጥጥር ስር የዋሉ ተጠርጣሪዎች ቢኖሩም በቂ ማስረጃ የተገኘባቸው ተጠርጣሪዎች በተቻለ ፍጥነት ክስ የተመሰረተባቸው መሆኑን፣ ከጀልዱ፣ ግንደበረት እና አቡነ ግንደበረት ውጪ በሌሎች አካባቢዎች በቂ ማስረጃ ያልተገኘባቸው ሰዎች ሕጉ በሚያዘው መሠረት የምርመራ መዝገቦቻቸው ተዘግተው መለቀቃቸውን ይገልጻል፡፡ ሁኔታዎች ከተረጋጉ በኋላ ጥቆማ የቀረበባቸው ተጠርጣሪዎች በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብቻ እንዲያዙ የተደረገ መሆኑን ካነጋገሩዋቸው የፖሊስ እና የዐቃቤ ሕግ ኃላፊዎች መረዳት መቻሉን መሥሪያ ቤቱ በምላሹ ጠቅሷል፡፡

ኢሰመኮ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንደሳ ግድያን ተከትሎ የተፈጠረው የሰላም መደፍረስ ሰፊ፣ ውስብስብ እና ምርመራውም ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ የሚችል መሆኑን ይረዳል፡፡ ይሁንና የክስ ሂደቱ ሲጀመር ብዛት ያላቸው ማስረጃ ያልተገኘባቸው ተጠርጣሪዎች ከእስር የተለቀቁ ቢሆንም ክትትሉ በሚደረግበት ወቅት በተለያዩ ፖሊስ ጣቢያዎች ክስ ሳይመሰረትባቸው በእስር ላይ ያሉ ሰዎች ነበሩ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ክትትሉ በተደረገበት ወቅት ጉዳያቸው የአርቲስቱን ግድያ ተከትሎ ከተፈጠረው የሰላም መደፍረስ ጋር የማይያያዝ "በወቅታዊ ሁኔታ" የተጠረጠሩ የሚባሉ ሰዎች ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተይዘው በሕግ ከተቀመጠው ጊዜ በላይ በእስር ላይ ነበሩ፡፡

በሌላ በኩል ኢሰመኮ ክትትል ካደረገባቸው የፖሊስ ጣቢያዎች መካከል በሦስቱ (በገደብ አሳሳ ሦስት ሰዎች፣ በዶዶላ ሦስት ሰዎች እና በአዳባ አራት ሰዎች) በድምሩ አሥር ተጠርጣሪዎች ያለፍላጎታቸው ወደ ሻሸመኔ ከተማ ተወስደው የታጣቂ ወይም የወታደር ልብስ እንዲለብሱ፣ አርቲፊሻል ፀጉር እንዲያደርጉ እና የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን እንዲይዙ ተደርገው ከዚያ በፊት ከማያውቋቸው ሰዎች ጋር በቪዲዮ ካሜራ መቀረጻቸውን ይናገራሉ፡፡ ስለሁኔታው የተጠየቁት የሁለት ፖሊስ ጣቢያዎች ኃላፊዎች እስረኞቹ ወደ ሻሸመኔ መወሰዳቸውን ያረጋገጡ ቢሆንም በካሜራ ስለመቀረጻቸው እንደማያውቁ ተናግረዋል፡፡ የአንድ ፖሊስ ጣቢያ ኃላፊ ተጠርጣሪዎቹ መቀረጻቸውን አምነው ነገር ግን የተቀረጹት የጦር መሳሪያ በመያዝ ሳይሆን ቀደም ሲል በሌላ ቦታ ወንጀል ፈጽመው አሁን ወደሚገኙበት ወረዳ የመጡ በመሆናቸው በፊት ከነበሩበት ወረዳ ጋር በቪዲዮ ኮንፈረንስ በማገናኘት መረጃ ለመሰብሰብ ነው ብሏል፡፡

በአንዳንድ ፖሊስ ጣቢያዎች በተለይም በገደብ አሳሳ ወረዳ የሚገኙ እስረኞች አንዳንድ የፖሊስ አባላት (በተለይም የልዩ ሀይል አባላት) ሰዎችን "ለጥያቄ ትፈለጋላችሁ" በሚል በሌሊት ጭምር ከቤት በመውሰድ በቁጥጥር ስር ካዋሉ በኋላ ገንዘብ የሚጠይቁና የሰጡትን በመልቀቅ ይህንን የማይፈጽሙ ሰዎችን ደግሞ "የኦነግ ሸኔ" አባል ወይም ደጋፊ ናችሁ በማለት እንከሳችኋለን በማለት ዛቻ እና ማስፈራርያ የሚያደርሱባቸው መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ የክትትል ቡድኑ ይህንን ቅሬታ በሌላ ገለልተኛ ማስረጃ ማረጋገጥ አልቻለም፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይህንን ጉዳይ በማስመልከት በሰጠው ምላሽ ይህ ሁኔታ እንዳይፈጠር የሚያስችል ጥብቅ የቁጥጥር ሥርዓት መኖሩን በማመልከት ቅሬታው "ከእውነት የራቀ" እንደሆነና ያም ሆኖ

ቅሬታው በማስረጃ ተደግፎ ከቀረበ ፈጻሚዎችን ለሕግ ለማቅረብ ዝግጁ መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጥቷል፡፡

በተወሰኑ ቦታዎች (ለምሳሌ በሻሸመኔ፣አዳባ) ከተለያዩ ጥቃቅን እና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት (WALQO, Vision fund ወዘተ) የተበደሩትን ገንዘብ ባለመመለሳቸው ወይም ገንዘቡን ተበድረው ላልመለሱ ሰዎች ዋስ በመሆናቸው ጋር በተያያዘ የፍትሐ ብሔር ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው በእስር ላይ የነበሩ ሰዎችን የክትትል ቡድኑ ተመልክቷል፡፡

### 3.2. የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ያለማክበር

ክትትል ከተደረገባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች መካከል በአብዛኞቹ ብዛት ያላቸው "በወቅታዊ ሁኔታ" ተጠርጥረው የታሰሩ ናቸው የተባሉ እስረኞች በፍርድ ቤት ዋስትና ተፈቅዶላቸው ወይም ለፍርድ ቤት የዋስትና ጥያቄ ማመልከቻ አስገብተው ፖሊስ ማመልከቻውን ፈርሞ በመቀበል እስረኛውን ፍርድ ቤት ማቅረብ ሲገባው ይህንን ባለማድረጉ የዋስትና ጥያቄያቸው በፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይሰጠው በመቅረቱ ከአሥራ አምስት ቀን እስከ አምስት ወራት ለሚሆን ጊዜ ያለ አግባብ በእስር ላይ የነበሩ መሆኑን ለክትትል ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

በዶዶላ 13 ተጠርጣሪዎች በዋስ እንዲለቀቁ ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መፈታት ሲገባቸው በእስር እንዲቆዩ ተደርጓል፡፡ በአርሲ ነጌሌ ፖሊስ ጣቢያ የአርቲስት ሃጫሉ ግድያን ተከትሎ ከተፈጠረው የሰላም መደፍረስ ጋር በተያያዘ በወንጀል ተጠርጥረው ከታሰሩ 16 ሰዎች መካከል የተወሰኑት ዋስትና የተፈቀደላቸው ቢሆንም ሳይፈቱ የቀሩ ሲሆን የተቀሩት የዋስትና ጥያቄያቸው የተለመደውን አሰራር ተከትሎ ወደ ፍርድ ቤት እንዳይደርስ በመደረጉ ለወራት በእስር ላይ ነበሩ፡፡ በኦለንጪቲ በፖሊስ ጣቢያ ከሚገኙ ሰዎች መካከል አንድ ተጠርጣሪ በዋስትና እንዲፈታ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ያስተላለፈ ቢሆንም ከእስር ሳይለቀቅ በሌላ ወንጀል ተጠርጥረሃል ተብሎ ለሁለት ወር ተኩል ክስ ሳይመሰረትበት በጣቢያው ታስሮ እንዳለ ለኢሰመኮ የክትትል ቡድን አስረድቷል፡፡ አንዳንድ እስረኞች ደግሞ የዋስትና ጥያቄ ፍርድ ቤት ካቀረብን ወደ ሌላ የማይታወቅ ቦታ ይወስዱናል በሚል ስጋት የዋስትና ጥያቄ ለመጠየቅም ፍራቻ እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡

በሌላ በኩል ዐቃቤ ሕግ "የአያስከስስም ውሳኔ" የሰጠባቸው ነገር ግን በእስር ላይ እንዲቆዩ የተደረጉ ተጠርጣሪዎች መኖራቸውን የክትትል ቡድኑ ተመልክቷል፡፡ በሻሸመኔ ወረዳ 2

ፖሊስ ጣቢያ የምትገኝ አንዲት እስረኛ በዋስ እንድትለቀቅ ፍርድ ቤት ያዘዘ እና ዐቃቤ ሕግም በተጠረጠረችበት ወንጀል የአያስከስም ውሳኔ በመስጠት እንድትለቀቅ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ከሦስት ወራት በላይ ከታሰረች በኂላ ሌላ አዲስ ወንጀል ተጠቅሶባት መከሰሷን እና በእስር እንድትቆይ መደረጓን በመናገር ያለፈችበትን ውጣ ውረድ "መንግሥት ሳይሆን ግለሰብ በግል ቂም አስሮኝ ያስቀመጠኝ ይመስለኝ ነበር" ስትል በፍርድ ቤቶች እና በዐቃቤ ሕግ የሚሰጡ ትዕዛዞች አለመከበራቸው በሕግ ሂደቱ ላይ ተስፋ አንዳስቆረጣት ለክትትል ቡድኑ ገልጻለች፡፡

በተለያዩ ክትትል በተደረገባቸው አከባቢዎች የሚገኙ የፖሊስ ጣቢያ ኃላፊዎች ለክትትል ቡድኑ ባደረጉት ገለጻ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች መኖራቸውን የሚያምኑ ቢሆንም "በወቅታዊ ሁኔታ" ምክንያት "ከበላይ አካል" በመጣ ትዕዛዝ መሠረት የታሰሩ ሰዎችን በሚመለከት ውሳኔ መስጠት የሚችሉት የወረዳ ወይም የዞን "ፀጥታ ምክር ቤቶች" መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ ያም ሆኖ በራሳቸው ውሳኔ መስጠት ባይችሉም እንኳን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የዞን እና የክልል አካላት ጋር በመነጋገር ረዘም ላለ ጊዜ በእስር ላይ የቆዩ ሰዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ወይም በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ወደ ማሰልጠኛ ካምፕ እንዲላኩ ለማድረግ ጥረት በማድረግ ላይ መሆናቸውን ለክትትል ቡድኑ አስረድተዋል፡፡ በተቃራኒው በክልሉ ካለው የፀጥታ ችግር አንጻር በፖሊስ እየተወሰደ ያለው እርምጃና የፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ አለመከበሩም ጭምር ምክንያታዊ እና ተገቢነት ያለው መሆኑን የሚገልጹ የፖሊስ ኃላፊዎችም ነበሩ፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይህንን ችግር በማስመልከት በሰጠው ምላሽ ችግሩ በተወሰነ ቦታዎች ማጋጠሙን በመጥቀስ ይህም "በወቅቱ ከነበረው የወንጀል ድርጊት መጠነ ሰፊነት፣ ከነበረው እረፍት አልባ የሥራ ጫና ይግባኝ እስከሚጠየቅ ድረስ ተጠርጣሪዎቹ ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ይፈጽማሉ ወይንም ይጠፋሉ ተብሎ ስለሚገመትና ከህብረተሰቡ ሰፊ ቅሬታ ይቀርብ ስለነበር በተጨማሪም በወቅቱ ከነበረው ሁኔታ አንጻር በራሳቸው ላይም ወንጀል ሊፈጸምባቸው ይችላል ተብሎ ስለተሰጋ" ያጋጠመ ክፍተት መሆኑን ይገልጻል፡፡ የተጠቀሱት ምክንያቶች በፍርድ ቤት በሚኖር ክርክር ሊቀርቡ የሚችሉ ቢሆንም በማናቸውም ሁኔታዎች በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲለቀቁ የተባሉ ሰዎችን በእስር ለማቆየት ምክንያት መሆን እንደሌለባቸው ኢሰመኮ ያምናል፡፡

### 3.3. እስረኞች ላይ የሚፈጸም ድብደባ እና ኢሰብአዊ አያያዝ

ኢሰመኮ ክትትል ባደረገባቸው በአብዛኞቹ የፖሊስ ጣቢያዎች (ለምሳሌ አዳሚ ቱሉ፣ አዳባ፣ አሳሳ፣ አርሲ ነጌሌ፣ አዳማ ዳቤ ሶሎቄ ፖሊስ ጣቢያ፣ ሮቤ ባሌ፣ ዴራ፣ ጭሮ፣ ኦለንጪቲ፣ ሀሮማያ ወ.ዘ.ተ.) የሚገኙ ብዛት ያላቸው እስረኞች መጠኑ እና መልኩ ቢለያይም በአብዛኛው በሚያዙበት ወቅት እንዲሁም ፖሊስ ጣቢያ ከገቡ በኋላ ድብደባ እና ሌሎችም ኢሰብአዊ አያያዝ እንደሚፈጸምባቸው እስረኞች ይገልጻሉ። በዚሁ ምክንያት ጭንቅላታቸው፣ ፊታቸው፣ አፍንጫቸው፣ ሆዳቸው፣ እግራቸው፣ ጥርሳቸው ወ.ዘ.ተ. ላይ ጉዳት ደርሶባቸው ገና ያልዳነ ቁስል፣ ስብራት ወይም ደም በሰውነታቸው ላይ የሚታይ እና ለጊዜያዊ እና ቋሚ የአካል ጉዳት የተዳረጉ እስረኞችን የኢሰመኮ የክትትል ቡድን ተመልክቷል።

ለምሳሌ በአሳሳ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ክትትሉ በተደረገበት ወቅት በጣቢያው ከነበሩ 110 (103 ወንድ እና 7 ሴት) እስረኞች መካከል ከ30 በላይ የሚሆኑት በሚያዙበት ወቅት ወይም በጣቢያው ውስጥ ከገቡ በኋላ በተፈጸመባቸው ድብደባ ምክንያት በተለያየ የሰውነታቸው ክፍል ላይ ቁስል፣ ጠባሳ እና ስብራት ይታይባቸው ነበር። ድብደባ ተፈጸመብን ያሉ እስረኞች የድርጊቱን ፈጻሚዎች ስም በመጥቀስ ጭምር ለኢሰመኮ የክትትል ቡድን አስረድተዋል። ድብደባ ከተፈጸመባቸው እስረኞች መካከል የተወሰኑት በግምት ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት እስከ ሌሊቱ 8፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ከቤታቸው በቁጥጥር ስር በዋሉበት ወቅት የተደበደቡ መሆናቸውን የገለጹ ሲሆን በቁጥጥር ስር በሚውሉበት ወቅትም ልጆቻቸው እና የትዳር አጋሮቻቸው ባሉበት መደብደባቸውን፣ የተወሰኑት ደግሞ ልጆቻቸው እና የትዳር አጋሮቻቸውም ጭምር መደብደባቸውን ተናግረዋል። ቅሬታውን ካቀረቡት መካከል 16 እስረኞች ከሚኖሩበት የገጠር ቀበሌ በግምት ከሌሊቱ 8፡00 ሰዓት ላይ ከቤታቸው በተያዙበት ወቅት ልዩ ፖሊሶች ፊታቸውን በልብስ እንዲሸፍኑ እና መሬት ላይ በሆዳቸው እንዲተኙ በማድረግ፣ ከዚያም በጀርባቸው ላይ በጫማ በመረጋገጥ እና "እንረሽናችኋለን" እያሉ በማስፈራራት ኢሰብዓዊ ድርጊቶችን እንደፈጸሙባቸው ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

በአዳባ ወረዳ አንዲት የምታጠባ እና እርጉዝ መሆኗን የገለጸች ሴት የ"ኦነግ ሸኔ" አባል ነው ተብሎ የሚፈለግ ባለቤቷን ለመያዝ የመጡ ፖሊሶች እሱን ባለማግኘታቸው ምክንያት እንደያዝዋት እና በወቅቱም ድብደባ እንደተፈጸመባት የገለጸች ሲሆን በሰውነቷ ላይ የድብደባ ምልክቶች ይታዩ ነበር።

በአርሲ ነጌሌ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ የክትትል ቡድኑ ጉብኝት ባደረገበት እለት በቤተሰብ ውስጥ በተፈጠረ ጥል ምክንያት በቁጥጥር ስር የዋለ መሆኑን የገለጸ አንድ ግለሰብ በሚያዝበት ወቅት በፖሊሶች ድብደባ እንደተፈጸመበት ለክትትል ቡድኑ ያስረዳ ሲሆን በወቅቱም ጉዳት ደርሶበት በፖሊስ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ መሬት ላይ ሲንከባለል ነበረ። ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች ተፈጸመብን ባሉት ድበደባ ምክንያት ለተለያዩ አካላዊ ጉዳቶች የተዳረጉ እስረኞችን የክትትል ቡድኑ ተመልክቷል።

በአዳሚ ቱሉ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ 23 እስረኞች በቁጥጥር ስር በዋሉበት ጊዜ እና ፖሊስ ጣቢያ ከገቡም በኋላ በወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት ኃላፊ ጭምር ድብደባ የተፈጸመባቸው መሆኑን ለኮሚሽኑ አስረድተዋል። በጉብኝቱ ወቅትም እግራቸው ላይ በደረሰባቸው ድብደባ ምክንያት የሚያነክሱ፣ እጃቸው የተሰበረ እና የተለያዩ የድብደባ ምልክቶች የሚታዩባቸው ተጠርጣሪዎች መኖራቸውን የኢሰመኮ የክትትል ቡድን ለማየት ችሏል። በዚሁ ፖሊስ ጣቢያ በግድያ ወንጀል የተጠረጠረ አንድ ታሳሪ ከአከባቢው ተሰውሮ ቆይቶ ሌላ ቦታ የተያዘ መሆኑን በምክንያትነት በመጥቀስ እንደገና እንዳያመልጥ በሚል ምክንያት በመኝታ ክፍሉ ውስጥ ጭምር እጁ በካቴና ታስሮ ነበር።

በአወዳይ እና ጭሮ ከተሞች በሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች ውስጥ በተፈጸመባቸው ድበደባ ምክንያት በተለያዩ የሰውነታቸው ክፍሎች ላይ ቁስል ወይም ጠባሳ ያለባቸው፣ እጃቸው ወይም እግራቸው የተሰበረ ተጠርጣሪዎች ልብሳቸውን ገልጠው ለኮሚሽኑ ባለሙያዎች አሳይተዋል።

በኦለንጪቲ ስምንት ተጠርጣሪዎች ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ከገቡ በኋላ በፖሊስ አባላት ድብደባ እንደተፈጸመባቸው የገለጹ ሲሆን ድርጊቱ ከተፈጸመባቸው ተጠርጣሪዎች መካከል አንድ ተጠርጣሪ የተጠረጠረበትን ወንጀል እንዲያምን የተደበደበ መሆኑን ገልጾ ይህንኑ ባለማድረጉ ምክንያት በወረዳው ለሚገኝ የኦሮሚያ ልዩ ኃይል ተላልፎ ተሰጥቶ ወደ ጫካ ተወስዶ ድብደባ እንደተፈጸመበት እና በዚሁ ምክንያት በጀርባው ላይ ቁስል መኖሩን ለክትትል ቡድኑ አሳይቷል። በጣቢያው የነበሩ ሌሎችም ተጠርጣሪዎች በሚያዙበት ወቅት እና ቃላቸውን ለመርማሪ ፖሊስ በሚሰጡበት ጊዜ ድብደባ እንደተፈጸመባቸው ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

የክትትል ቡድኑ ስለ ጉዳዩ የጠየቃቸው አብዛኛዎቹ የጣቢያዎቹ ኃላፊዎች ከፖሊስ ጣቢያ ውጪ በልዩ ፖሊስ የተፈጸመ ድብደባን በማስመልከት የተነሱ ቅሬታዎች ከስልጣናቸው ውጪ ስለሆኑ በጉዳዩ ላይ አስተያይት መስጠት የማይችሉ መሆኑን ጠቅሰው ያም ሆኖ ግን አንዳንድ

ጊዜ ተጠርጣሪዎች በሚያዙበት ወቅት ለማምለጥ ሲሞክሩ ፖሊሶች እርምጃ ወስደው ሊሆን እንደሚችል ግምታቸውን ያስቀመጡ ሲሆን በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ድብደባ ይፈጸምብናል በሚል የቀረበውን ቅሬታ ግን አስተባብለዋል፡፡

የተወሰኑ ጣቢያዎች ኃላፊዎች ደግሞ (ለምሳሌ ጭሮ) በጣቢያቸው ችግሩ ካለ አጣርተው የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወስዱ ቃል ገብተዋል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ አንዳንድ የፖሊስ ጣቢያ ኃላፊዎች (ለምሳሌ በአሳሳ፣ አዳማ ዳቤ ሶሎቄ ክፍለ ከተማ፣ ዶዶላ) ችግሩ በተጠርጣሪዎቹ "የአደገኝነት ባህሪ" ምክንያት የተከሰተ ሊሆን ይችላል የሚል አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ ከተፈጠረው ከፍተኛ የፀጥታ ችግር አንጻር "በተለመደው መንገድ የሕግ የበላይነትን ለማስከበር የማይቻል" በመሆኑና ችግሩ "በአከባቢው ከነበረው የፖሊስ ሀይል አቅም በላይ ስለነበር ሊደርስ የነበረውን ጥፋት በማስቀም ሂደት "አንዳንድ የመብት ጥሰቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ አይካድም" በሚል ምላሽ የሰጠ ሲሆን ያም ሆኖ ጉዳት የደረሰው ለሕግ አልገዛም ያሉትንና በጉልበት ከፀጥታ ሀይሎች ላይ መሳሪያ ለመንጠቅ የሞከሩ ተጠርጣሪዎችን ተመጣጣኝ ሀይል በመጠቀም በቁጥጥር እንዲውሉ በማድረግ ሂደት መሆኑን ገልጿል፡፡ በተጨማሪም የተወሰኑ ተጠርጣሪዎች ለማምለጥ ሲሮጡ ወድቀው የተጎዱ መሆኑን እንዲሁም በተፈጠረው የሰላም መደፍረስ ውስጥ በፍንዳታ እና በእሳት ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን በመጥቀስ በፖሊስ የተደበደበ እስረኛ አለመኖሩን ይገልጻል፡፡

ኢሰመኮ የሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በነበረው መጠነ ሰፊ የሰላም መደፍረስ ምክንያት የተፈጠሩ ውስብስብ ሁኔታዎችን እና ልዩ ተግዳሮቶችን በሚገባ ይረዳል፡፡ ይሁንና እነዚህ ተግዳሮቶች ቢኖሩም የሰብአዊ መብቶችን የማክበር አስፈላጊነትን የማያስቀሩ በመሆኑ የሕግ አስከባሪ አካላት በአስቸጋሪ ሁኔታዎችም ውስጥ ቢሆን ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል በሚያዙበት ወቅት በልዩ ሀይል በተፈጸመባቸው ድብደባ የተለያዩ አካላዊ ጉዳቶች የደረሱባቸው መሆኑን ለክትትል ቡድኑ ያሳዩ አብዛኞቹ እስረኞች የአርቲስቱን ግድያ ተከትሎ ከተፈጠረው የሰላም መደፍረስ በኋላ በተለያዩ ጊዜያት "በወቅታዊ ሁኔታ" በሚል በቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች መሆናቸውን ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

### 3.4. ሰዎችን ስለ ሌሎች ተጠርጣሪዎች ማሰር

ለወንጀል ድርጊት የግል ተጠያቂነት መርህን (principle of individual responsibility) በሚጻረር መልኩ "በወንጀል ተጠርጥረው የሚፈለጉ ልጆቻችሁን አምጡ" በሚል አባት ወይም እናትን ማሰር እንዲሁም "ባልሽን አምጪ" በማለት ሚስትን የማሰር ሁኔታዎች መኖራቸውን ኢሰመኮ ባደረገው ክትትል እና በየጊዜው ከሚደርሱት አቤቱታዎች ለመረዳት ችሏል።

በዚሁ ሁኔታ የታሰሩ መሆኑን የገለጹ የሚያጠቡ እናቶችን እና እርጉዝ ሴቶችን የክትትል ቡድኑ ተመልክቷል። ለምሳሌ በአወዳይ ከተማ ሦስት ሴቶች በወንጀል የሚፈለጉ (በፖሊስ አመራሮቹ አገላለጽ "የኦነግ ሸኔ" አባላት) ልጆቻችሁን አቅርቡ በሚል የታሰሩ መሆኑን እና አንዲት ሴት ባልሽን አቅርቢ በሚል ከሕጻን ልጇ ጋር በእስር እንደምትገኝ ለመረዳት ተችሏል። በተመሳሳይ መልኩ በአዳባ ፖሊስ ጣቢያ "በኦነግ ሸኔ" አባልነት ተጠርጥሮ የሚፈለግ ባሏ ከፖሊሶች በመሰወሩ ምክንያት የታሰረች መሆኑን የገለጸች አንዲት እርጉዝ ሴት ሕጻን ልጇን ይዛ በእስር ላይ ነበረች። በአንዳንድ ፖሊስ ጣቢያዎች (ለምሳሌ ዶዶላ) "በወቅታዊ ሁኔታ" የተጠረጠሩ ናቸው የተባሉ ባልና ሚስት ሕጻናት ልጆቻቸውን ይዘው በእስር ላይ የነበሩ መሆኑን የክትትል ቡድኑ ተመልክቷል።

በግንደበረት ፖሊስ ጣቢያ በ"ኦነግ ሸኔ" አባልነት ተጠርጥረው የሚፈለጉ ልጆቻችሁን አቅርቡ ተብለው የታሰሩ መሆናቸውን የገለጹ ባልና ሚስት የሆኑ ወላጆችን ጨምሮ 4 አባቶች እና 2 እናቶች በእስር ላይ ነበሩ። የክትትል ቡድኑ ስለ ጉዳዩ ያነጋገራቸው አንዳንድ የፖሊስ ጣቢያ አመራሮች ዋናዎቹን ተጠርጣሪዎች ለመያዝ ይህንን ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን የተናገሩ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ (ለምሳሌ አዳባ) በተለይም በወንጀል ተጠርጥረው ከሚፈለጉ ልጆቻቸው ወይም ባሎቻቸው ጋር በተያያዘ የታሰሩ እናቶችን ወይም ባለትዳር ሴቶችን በተመለከተ በሰጡት አስተያየት ልጆቻቸው ወይም ባሎቻቸው በወንጀል የሚፈለጉ ቢሆኑም ግለሰቦቹ የታሰሩት በወንጀሉ ተሳትፎ ስላላቸው እና በግል ስለሚጠየቁም ጭምር መሆኑን ያስረዳሉ።

የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይህንን ቅሬታ በማስመልከት በሰጠው ምላሽ የተጠርጣሪዎች ቤተሰቦች ተጠርጣሪዎችን አቅርቡ በሚል ይታሰራሉ የተባለው ትክክል እንዳልሆነና በምሳሌነት በተጠቀሱት ፖሊስ ጣቢያዎች ያሉት ሰዎች የታሰሩት እራሳቸው ወንጀል ፈጽመዋል በሚል እንጂ ተጠርጣሪዎችን አምጡ በሚል እንዳልሆነ ፖሊስ ጣቢያዎቹ በመገኘት አረጋግጠናል

የሚል ምላሽ ሰጥቷል። ይህ ቅሬታ በክትትሉ ወቅት በተለያዩ ፖሊስ ጣቢያዎች በሚገኙ እስረኞች በተደጋጋሚ የተነሳ ጉዳይ እንደመሆኑና አንዳንድ የፖሊስ ጣቢያዎች ኃላፊዎች (ተወካዮች) ጭምር ዋናዎቹን ተጠርጣሪዎች ለመያዝ ይህንን ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ አሰራሩን ደግፈው የተናገሩ በመኖራቸው ኢሰመኮ አሁንም ቢሆን ጉዳዩን በጥልቀት ማጣራት እንደሚያስፈልግ ያምናል። ይህ አሰራር ሕገ ወጥ ከመሆኑም ባሻገር ለመብት ጥሰት ተጋላጭ በሆኑ ሴቶች እና ሕጻናት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ያለው እንደመሆኑም በአንክሮ ሊመረመር ይገባዋል።

### 3.5. "የፀጥታ ምክር ቤቶች" እና ፍትሕ የማግኘት መብት

የኢሰመኮ የክትትል ቡድን ከተለያዩ የፖሊስ ጣቢያ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ውይይት "በወቅታዊ ሁኔታ" የተጠረጠሩ ሰዎችን ጉዳይ በተመለከተ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያላቸው በዞን እና በወረዳ ደረጃ የተቋቋሙ "የፀጥታ ምክር ቤቶች" (Mana maree nageenyaa) መሆናቸውን ተረድቷል። "የፀጥታ ምክር ቤት" አምስት አባላት ያሉት ሲሆን እነሱም የዞን ወይም የወረዳ አስተዳዳሪ ወይም የከተማ ከንቲባ (ሰብሳቢ)፣ የዞን ወይም የወረዳ የብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ (ምክትል ሰብሳቢ)፣ የዞን ወይም የወረዳ የአስተዳደር እና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ (አባል)፣ የዞን ወይም የወረዳ ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ (አባል)፣ የዞን ወይም የወረዳ የዐቃቤ ሕግ ቢሮ ኃላፊ (አባል) ናቸው።

ከኃላፊዎቹ ገለጻ ለመረዳት እንደተቻለው ምክር ቤቱ የአካባቢውን ወቅታዊ የሰላም ሁኔታ በመገምገም መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች አቅጣጫ ከማስቀመጥ በተጨማሪ በቁጥጥር ስር መዋል ያለባቸው ተጠርጣሪዎችን ይወስናል፣ እንዲሁም ከእስር መለቀቅ ያለባቸው ተጠርጣሪዎችን በመለየት ውሳኔ ይሰጣል። በመሆኑም "በወቅታዊ ሁኔታ" የተጠረጠሩ ሰዎችን በሚመለከት በፍርድ ቤቶችም ሆነ በዐቃቤ ሕግ የሚሰጡ ውሳኔዎች ተፈጻሚ ለመሆን የምክር ቤቱን ይሁንታ ማግኘት ያለባቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

ይህ አሰራር ተጠርጣሪዎች ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ፣ ከታሰሩም በኋላ በሕግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ፍርድ ቤት ቀርበው ጉዳያቸው በገለልተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ የተፋጠነ ፍትሕ እንዳያገኙ እንዲሁም በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎች ተፈጻሚ እንዳይሆኑ በማድረግ ሰዎችን በሕግ ከመዳኘት ይልቅ የፖለቲካ ውሳኔዎች ሰለባ እንዲሆኑ ያደርጋል።

ኢሰመኮ በተለያዩ ፖሊስ ጣቢያዎች ያነጋገራቸው በፍርድ ቤት የተሰጣቸው ውሳኔዎች በምክር ቤቱ እንዳይፈጸሙ በመደረጋቸው ምክንያት ለወራት በእስር ላይ የቆዩ ተጠርጣሪዎች በፍትሕ ስርዓቱ ተዓማኒነት ላይ ሰፊ ጥያቄ ያነሳሉ። የክልሉ መንግሥት የህዝብን ሰላም እና ደህንነት የማስጠበቅ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ባይዘነጋም ይህንኑ ኃላፊነት ለመወጣት የሚወሰዱ እርምጃዎች በሕገ መንግሥቱ የተቋቋሙ የፍትሕ ተቋማትን ስልጣን እና ተግባርን ያከበሩ መሆን አለባቸው።

### 3.6. በእስር ላይ የሚገኙ ሴቶች እና ሕጻናት

ክትትሉ በተደረገባቸው በሁሉም ፖሊስ ጣቢያዎች ሴት እስረኞች ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል ራሳቸው በወንጀል ተጠርጥረው የታሰሩ ወይም ሌላ በወንጀል የሚፈለግ የተሰወረ የቤተሰብ አባል አቅርቡ ተብለው የታሰሩ መሆናቸውን የሚገልጹ ሴቶች ነበሩ። ከነዚህ ሴቶች መካከል የተወሰኑት እድሜያቸው ከ 5 ወር እስከ 10 ዓመት የሚሆናቸው ሕጻናት ልጆችን ይዘው የታሰሩ ናቸው።

በሻሸመኔ ወረዳ ሁለት ፖሊስ ጣቢያ በእስረኛ አጅግ በተጨናነቀ፣ ሰፊ የንጽህና ጉድለት በሚታይበት እና ከኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ቫይረስ ጋር የምትኖር እስረኛን ጨምሮ የተለያዩ ታማሚዎች ባሉበት ክፍል ውስጥ በተለያዩ ወንጀሎች ተጠርጥረው ከታሰሩ እናቶቻቸው ጋር በእስር ላይ የሚገኙ እድሜያቸው ከ3 ዓመት እስከ 10 ዓመት የሚሆን 8 ሕጻናትን የክትትል ቡድኑ ተመልክቷል። በአዳባ እና ሮቤ ባሌ ከተማ ፖሊስ ጣቢያዎች እድሜያቸው ከ 5 ወር እስከ አንድ ዓመት የሚሆናቸው ሕጻናትን የያዙ እናቶች እንዲሁም በዶዶላ አንዲት እናት ከባለቤቷ ጋር ሕጻን ልጇን ይዛ በእስር ላይ የምትገኝ መሆኑን የክትትል ቡድኑ ተመልክቷል።

በአወዳይ ሴት ተጠርጣሪዎች ከወንድ ተጠርጣሪዎች ጋር አንድ ግቢ ውስጥ ይገኛሉ። በጭሮ ሴት ተጠርጣሪዎች ለደህንነታቸው አስጊ በሆነ ሁኔታ መጸዳጃ እና መታጠቢያ ቤቶችን ከወንዶች ጋር ይጠቀማሉ። በሌላ በኩል በወንጀል ተጠርጥረው የታሰሩ ሕጻናት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 172 መሠረት ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ በዋስ እንዲለቀቁ ቢጠበቅም፤ ከዚህ በተቃራኒ በተለያዩ ፖሊስ ጣቢያዎች በወንጀል ጉዳይ ተሳታፊ ናቸው በሚል የተጠረጠሩ እድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት አካለ መጠን ከደረሱ እስረኞች ጋር ተቀላቅለው በእስር ላይ ይገኛሉ። ለምሳሌ በአዳሚ ቱሉ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ 6፣

በኦለንጪቲ 4፣ በአርሲ ነጌሌ 1፣ በአዳባ 2 በወንጀል ጉዳይ ተሳታፊ ናቸው በሚል የተጠረጠሩ ሕጻናት አካለ መጠን ከደረሱ ሰዎች ጋር አንድ ላይ ታስረው የክትትል ቡደኑ ተመልክቷል።

ከእናቶቻቸው ጋር የታሰሩ ወይም በወንጀል ጉዳይ ተሳታፊ ናቸው በሚል ተጠርጥረው የተያዙ ሕጻናት በእስር ቤቶቹ በቂ ምግብ አያገኙም። የማቆያ ክፍሎቹም ከፍተኛ የንጽህና ጉድለት ያለባቸው እና ፍራሽ ወይም ሌላ ለመተኛት የሚያገለግል ቁሳቁስ የሌላቸው በመሆኑ ሕጻናት እና እናቶች ከሲሚንቶ በተሰራ ወለል ላይ አንሶላ፣ ማዳበሪያ፣ ካርቶን እና የመሳሰሉ ነገሮችን በማንጠፍ ይተኛሉ። በዚሁ ምክንያት ሰውነታቸው በእጅጉ የተጎሳቆለ እና ለተለያዩ የቆዳ በሽታዎች የተጋለጡ ሕጻናትን የክትትል ቡድኑ ተመልክቷል።

### 3.7. የማቆያ ክፍሎች እጥረት እና የንጽህና ጉድለት

የኢሰመኮ የክትትል ቡድን የተመለከታቸው አብዛኞቹ ፖሊስ ጣቢያዎች የማቆያ ክፍሎች በእስረኛ የተጣበቡ ናቸው። ምልከታ ከተደረገባቸው ቦታዎች መካከል በአሰላ ወረዳ አንድ ፖሊስ ጣቢያ እና ሮቤ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ በአንጻራዊነት የተሻለ ሁኔታ ያለ ቢሆንም በተቃራኒው ደግሞ በሻሸመኔ፣ አሳሳ፣ አዳባ፣ ዱራ፣ ኦለንጪቲ፣ አወዳይ፣ ሀሮማያ፣ አዳሚ ቱሉ፣ ባቱ፣አቡነ ግንደበረት፣ ግንደበረት፣ ጀልዱ እና አርሲ ነጌሌ ከፍተኛ መጨናነቅ መኖሩን ለመረዳት ተችሏል። በእነዚህ ጣቢያዎች የቤቶቹ ስፋት ከእስረኞች ብዛት አንጻር ሲታይ ለአንድ ሰው ያለው ቦታ ከአንድ ካሬ በታች በመሆኑ እስረኞች ለመተኛት ብቻም ሳይሆን ለመቀመጥም ይቸገራሉ።

በዚሁ ምክንያት በአንዳንድ ጣቢያዎች የሚገኙ እስረኞች በቀን ከማረፍያ ክፍሎቹ በረንዳ ላይ ወይም ግቢ ውስጥ በመዋል ምሽት ላይ ደግሞ በተራ የሚተኙ መሆኑን ለክትትል ቡድኑ አስረድተዋል። አንዳንድ ጣቢያዎች ደግሞ በደህንነት ስጋት ምክንያት እስረኞች ከክፍሎቻቸው ወደ በረንዳ እንዲወጡ የማይፈቅዱ በመሆኑ እስረኞች አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ተደራርበው በመቀመጥ ቀንም ሆነ ምሽት በተጣበቡ ክፍሎች ውስጥ የሚያሳልፉ መሆኑን እስረኞቹ ለክትትል ቡድኑ አስረድተዋል።

በሻሸመኔ ወረዳ 2 ፖሊስ ጣቢያ የወንዶች ክፍል ስፋቱ በግምት 56 ካሬ ሜትር ሲሆን በክትትሉ ወቅት 73 ተጠርጣሪዎች ይገኙበት ነበር። የሴቶች ክፍል በግምት 24 ካሬ ሜትር የሚሆን ሲሆን 27 ተጠርጣሪዎችና 8 ሕጻናት ነበሩበት። በባቱ ፖሊስ ጠቢያ ለማደሪያነት

የሚያገለግሉ ሦስት ክፍሎች አሉ። በአንደኛው ክፍል 27 እስረኞች ያሉበት ሲሆን ስፋቱም በግምት 20 ካሬ ሜትር፣ በሁለተኛው ማደሪያ ክፍል 18 እስረኞች ያሉበት ሲሆን ስፋቱም በግምት 12 ካሬ ሜትር፣ በሦስተኛው ክፍል (የሴቶች) 4 እስረኞች ያሉበት ሲሆን ስፋቱም በግምት 5 ካሬ ሜትር ይሆናል። ከእስረኞች ጋር በተደረገው ውይይት በሦስቱም የማደሪያ ክፍሎች የሚገኙ እስረኞች ከፍተኛ መጨናነቅ መኖሩን በምሬት ያነሱ ሲሆን አንዳንዴም ያለው ቦታ ለሁሉም እስረኞች ስለማይበቃ በፈረቃ እንደሚተኙ አስረድተዋል። በጣቢያው ከፍተኛ መጣበብ በመኖሩ እና የአየር ፀባዩም ሞቃታማ በመሆኑ እስረኞቹ ለተለያዩ የቆዳ በሽታዎች መጋለጣቸውን የክትትል ቡድኑ ተመልክቷል።

በሀሮማያ የፖሊስ ጣቢያው ክፍሎች ከመጨናነቃቸው የተነሳ በርካታ እስረኞች በረንዳ ላይ ዳስ ጥለው እንደማረፊያ ይገለገሉበት ነበር። የማረፊያ ክፍሎቹ አየር የማያስገቡ እና በቂ ብርሃን የሌላቸው ናቸው። በአወዳይም ተመሳሳይ ችግሮች አሉ። በአቡነ ግንደበረት ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ 68 ወንዶች እስረኞች ሙሉ በሙሉ በቆርቆሮ በተሰሩ እና እያንዳንዳቸው በግምት 25 ስኩዌር ሜትር ያህል ስፋት ባላቸው 2 ክፍሎች ውስጥ ተይዘው ይገኙ ነበር።

በጣቢያዎቹ ያለው የማቆያ ክፍሎች ጥበት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብዙ ሰዎች በዘመቻ መልክ “በወቅታዊ ሁኔታ” ምክንያት በመታሰራቸው፣ ዋስትና የተፈቀደላቸው ሰዎች በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት ሳይለቀቁ ታስረው እንዲቆዩ በመደረጉ፣ ክስ የተመሰረተባቸው ወይም የተፈረደባቸው እስረኞች ወደ ማረሚያ ቤት መዘዋወር ሲገባቸው የኮቪድ-19 የምርመራ ኪት እጥረት በማጋጠሙ ምክንያት በወቅቱ ሳይዘዋወሩ በመቅረታቸው ምክንያት የተባባሰ መሆኑን የክትትል ቡድኑ ከእስረኞች እና ከጣቢያዎቹ ኃላፊዎች ጋር ካደረገው ውይይት ለመገንዘብ ችሏል።

በእስረኞች በተደጋጋሚ የተነሳ እና የክትትል ቡድኑም የተመለከተው ሌላው ጉዳይ የታሳሪዎች ማቆያ ክፍሎች እና የማቆያ ቦታዎች ግቢ የንጽህና ችግር ነው። ክትትል የተደረገባቸው ሁሉም የፓሊስ ጣቢያዎች ለማለት በሚቻል መልኩ ለመተኛት የሚያገለግል ፍራሽ የላቸውም፤ የክፍሎቹ ግድግዳዎች እጅግ የቆሸሹ እና ለብዙ አመታት ቀለም ያልተቀቡ በመሆናቸው በተባይ የተወረሩ እና ለሰው ልጅ ጤና እና መኖርያነት እጅግ የማይመች ደረጃ ላይ የደረሱ ናቸው። ለምሳሌ በአዳባ ፖሊስ ጣቢያ ለቢሮ የሚያገለግለው ህንጻ የውጪ እና የውስጥ ግርግዳው በጥሩ ሁኔታ ቀለም የተቀባ ቢሆንም በተቃራኒው እስረኞች ያሉባቸው

ሁሉም ክፍሎች ቀለም ሳይቀቡ ዘመናትን ያስቆጠሩ መሆኑን በቆሻሻ ከጠቆሩ ግድግዳዎች እና በግድግዳዎቹ ላይ ከተሳሉ የደርግ ዘመን ምልክቶች መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በአብዛኞቹ የፖሊስ ጣቢያዎች ግቢ ውስጥ የተከማቸ ቆሻሻ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ በአወዳይ እና በሻሸመኔ ወረዳ 2 ፖሊስ ጣቢያዎች ከተጠርጣሪዎች ማደሪያ ክፍል ጎን ብዙ ቆሻሻ ተከምሮ በመቆየቱ እስረኞች ለተለያዩ የመተንፈሻ አካላት በሽታዎች እየተዳረጉ መሆናቸውን በመጥቀስ ለክትትል ቡድኑ ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ የክትትል ቡድኑ ያነጋገራቸው አመራሮች ለክፍሎቹ ማስፋፍያ እና እድሳት ለማድረግ እና የተባይ ማጥፍያ ለመርጨት የበጀት እጥረት ያለባቸው መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ ይሁንና የበጀት እጥረቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ለችግሩ በቂ ትኩረትም ያልተሰጠው መሆኑን ከአመራሮች ጋር ከነበረው ውይይት መረዳት ይቻላል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በፖሊስ ጣቢያዎቹ ያለውን የማቆያ ቦታዎች ጥበት እና መጨናነቅ በማስመልከት በሰጠው ምላሽ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያ በድንገት የተፈጠረ ክስተት በመሆኑ ብዛት ያላቸው ተጠርጣሪዎችን ለመያዝ የሚችል የማቆያ ቦታ ባለመዘጋጀቱ ችግሩ የተፈጠረ መሆኑን በመጥቀስ ችግሩን በመቅረፍ ረገድ የተለያዩ ጥረቶች መደረጋቸውን ይገልጻል፡፡

### 3.8. የምግብ፣ የሕክምና እና የውሃ አገልግሎት

ኢሰመኮ ክትትል ባደረገባቸው ሁሉም የፖሊስ ጣቢያዎች የሚገኙ ተጠርጣሪዎች በመንግሥት ምግብ እንደማይቀርብላቸው በተለይም ከተለያዩ የገጠር ቀበሌዎች ተይዘው ክስ ሳይመሰረትባቸው ለረጅም ጊዜ በፖሊስ ጣቢያ የሚገኙና ቤተሰባቸው በአቅም ማነስ ወይም የመኖርያ አድራሻቸው ሩቅ በመሆኑ ምክንያት ምግብ የማይቀርብላቸው ተጠርጣሪዎች በሌሎች እስረኞች ድጋፍ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እየኖሩ መሆኑን ለክትትል ቡድኑ ተናግረዋል፡፡ የፖሊስ ጣቢያዎቹ ኃላፊዎች ችግሩ መኖሩን ያረጋገጡ ቢሆንም ለፖሊስ ጣቢያዎቹ ለምግብ ተብሎ የሚመደብ በጀት የሌለ በመሆኑ መፍትሄ አጥተው የተቸገሩ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በጉዳዩ ላይ በሰጠው ምላሽ ፖሊስ ከአካባቢው መስተዳድር ጋር በመሆን ራሳቸውን መመገብ ያልቻሉ እስረኞች ምግብ እንዲያገኙ ሲያደርግ መቆየቱን

ይገልጻል። ይሁንና ክትትሉ በተደረገበት ወቅት በርካታ "በወቅታዊ ሁኔታ" ተጠርጥረው ከተለያዩ የገጠር ቀበሌዎች ተይዘው በየፖሊስ ጣቢያው በእስር ላይ የነበሩ ሰዎች በመንግሥት የሚቀርብላቸው ምግብ አልነበረም።

በሁሉም የፖሊስ ጣቢያዎች በመንግሥት የሚሰጥ ነጻ የጤና አገልግሎት የለም። እስረኞች የጤና አገልግሎት ወጪያቸውን በግል ይሸፍናሉ። አገልግሎቱን በሚመለከት ክትትሉ በተደረገባቸው ጣቢያዎች በስፋት የተነሳው ችግር እስረኞች የሕክምና አገልግሎት ጥያቄ በሚያቀርቡበት ወቅት አገልግሎቱን በጊዜ የማያገኙ መሆኑ ነው። አንዳንዶም ፖሊሶች እስረኞችን ወደ ሕክምና ተቋም ለመውሰድ ከ ብር 150 እስከ ብር 300 ድረስ የውሎ አበል ክፍያ እንደሚጠይቁና ለተጨማሪ ሕክምና ወደ ሌላ የሕክምና ተቋም እንዲሄዱ የሐኪም አስተያየት ሲሰጥም፤ ወደ ተላኩበት የጤና ተቋም በጊዜ እንደማይወሰዱ እስረኞች ቅሬታቸውን ያቀርባሉ።

በአርሲ ነጌሌ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ እስረኞች ህመም እየታየባቸው እንኳን የሕክምና ጥያቄ ሲያቀርቡ በጊዜ ሕክምና የማያገኙ መሆኑን እንዲያውም ጥያቄ ሲጠይቁ አንዳንድ የፖሊስ አባላት "ለምን አትሞቱም" እያሉ እንደሚሳለቁባቸው፣ ጥያቄውን በተደጋጋሚ በማንሳታቸው ድብደባ የተፈጸመባቸው ግለሰቦችም መኖራቸውን እስረኞች ለክትትል ቡድኑ ገልጸዋል። የክትትል ቡድኑ በጣቢያው በነበረበት ወቅት አንድ ተጠርጣሪ "በፖሊሶች በተፈጸመበት ድብደባ" የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቹ ላይ ጉዳት ደርሶበት ሕክምና ሳያገኝ መሬት ላይ ሲንከባለል የነበረ መሆኑን የክትትል ቡድኑ ተመልክቷል።

በሻሸመኔ ወረዳ 2 ፖሊስ ጣቢያ አንዲት ከኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ቫይረስ ጋር የምትኖር እስረኛ እና የሚጥል በሽታ ያለባት ሌላ እስረኛ በቋሚነት የሚወሰዱ በቂ መድሃኒት ባለማግኘታቸው ምክንያት በተደጋጋሚ የሚታመሙ መሆኑን ታማሚዎቹ እና አብረዋቸው ታስረው የሚገኙ ሌሎች እስረኞች ለክትትል ቡድኑ አስረድተዋል። በኦለንጪቲ አንድ ተጠርጣሪ የኤች. አይ. ቪ. የእድሜ ማራዘሚያ እና የሳንባ በሽታ መድሃኒትቶችን በቋሚነት የሚወስድ መሆኑን ገልጾ ከቤቱ ሲያዝ መድሃኒቱን ሳይወስድ ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመወሰዱ እና ወደ ጤና ተቋም ሄዶ መድሃኒት ማግኘት እንዲችል ፖሊሶችን ቢጠይቅም ወደ ጤና ተቋም ባለመወሰዱ ለ 15 ቀናት መድሃኒት ሳያገኝ በመቆየቱ ህመሙ እየተባባሰበት መምጣቱን ለክትትል ቡድኑ አስረድቷል።

በአሳሳ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ አንድ "በወቅታዊ ሁኔታ" ተጠርጥሮ ከትዳር አጋሩ ጋር የታሰረ የስኳር በሽተኛ ከወር በላይ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ የታሰረ መሆኑንና ከበሽታው ጋር የሚስማማ ምግብ እና በቋሚነት የሚወስዳቸውን መድሃኒቶች የሚያቀርብለት ሰው በማጣት በህመም እየተሰቃየ መሆኑን ለክትትል ቡድኑ አስረድቷል። የጣቢያዎቹ አመራሮች በበኩላቸው ያሉባቸው የሎጂስቲክ እና የሰው ሀይል እጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ የሕክምና አገልግሎት ጠይቆ የተከለከለ እስረኛ አለመኖሩን ገልጸው ነገር ግን አንዳንድ እስረኞች "ሳይታመሙ ለመውጣት ብቻ" ጥያቄ ያቀርባሉ፣ አንዳንዴ ደግሞ "ለማምለጥም ሊጠቀሙበት ይችላሉ" የሚል ስጋት ስላላቸው የሕክምና ጥያቄ ሲቀርብ በአግባቡ ማጣራት አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳሉ።

እስረኞች ወደ ጤና ተቋም ለመሄድ ለፖሊሶች ገንዘብ እንድንሰጥ እንጠየቃለን ያሉትን በሚመለከት ሁሉም አመራሮች ቅሬታውን ያስተባበሉ ሲሆን ያም ሆኖ አንዳንድ ጊዜ እስረኞችን ወደ ጤና ተቋም ለመውሰድ ፖሊስ ጣቢያዎቹ ተሽከርካሪ ስለሌላቸው ገንዘብ ያላቸው እስረኞች እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችላሉ የሚል ምላሽ ተሰጥቷል። ኃላፊዎቹ ያነሱት ነጥብ እንደተጠበቀ ሆኖ በአሰራር ደረጃ መደበኛ የሕክምና ጥያቄ ማቅረቢያ መንገድ (ቅጽ) አለመኖሩ፣ የሕክምና አገልግሎት ጥያቄ ሲቀርብ ደግሞ መቼ እንደ ቀረበ፣ ምን መልስ እንደተሰጠው እና ጠያቂው ተገቢ የሆነ መልስ ባይሰጠው ምን ማድረግ እንዳለበት በግልጽ የተቀመጠ የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩ ተጨማሪ ክፍተት እንደፈጠረ መረዳት ይቻላል።

የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ ክፍተቶች ያሉ ቢሆንም በተቻለ መጠን እስረኞች ሕክምና እንዲያገኙ እየተደረገ መሆኑን ይገልጻል።

ክትትል የተደረገባቸው አብዛኞቹ ፖሊስ ጣቢያዎች የመቆራረጥ ሁኔታ ቢኖርበትም የውሃ አቅርቦት አላቸው። ሆኖም በአንዳንድ ጣቢያዎች (ለምሳሌ በሀሮማያ) የወንዶችም ሆነ የሴቶች የገላ መታጠቢያ ቦታ የሌላቸው በመሆኑ በተለይም የሴት እስረኞች መቸገራቸውን ለክትትል ቡድኑ አስረድተዋል። በአወዳይ ፖሊስ ጣቢያ የግል ንጽህና ለመጠበቅ የሚያስችል የውሃ አቅርቦት የሌለ በመሆኑ በጣቢያው ያሉ እስረኞች የግል ንጽህና ለመጠበቅ ካለመቻል አልፎ በተባይ እንደሚቸገሩ የክትትል ቡድኑ ተመልክቷል።

### 3.9. የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት

ክትትሉ የተደረገባቸው አብዛኞቹ ፖሊስ ጣቢያዎች የንጽህና ጉድለት ያለባቸው ቢሆንም የመጸዳጃ ቤት አላቸው:: ነገር ግን ወጥ የሆነ የመጸዳጃ ቤት አጠቃቀም ስርዓት አለመኖሩን በመጥቀስ በተወሰኑ ቦታዎች እስረኞች ቅሬታዎችን አቅርበዋል:: አሁን ባለው ሁኔታ የመጸዳጃ ቤት መጠቀሚያ ጊዜ በየጣቢያው ባለው አመራር ይወሰናል:: በአብዛኞቹ ጣቢያዎች (ለምሳሌ አሳሳ፣ ዶደላ፣ አሰላ ወረዳ 1 እና አሰላ ወረዳ 2) በቀን ሁለት ጊዜ (ጧት እና ማታ) እስረኞች የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል:: ከዚህ በተጨማሪ በእነዚህ ጣቢያዎች እስረኞች በቀን ለውሃ ሽንት በማቆያ ክፍሎች ውስጥ ወይም በር ላይ በሚቀመጥ እቃ (ጄሪካን፣ ባልዲ፣ የውሃ ላሲቲክ ወዘተ.) ከሚጠቀሙት እና አንዳንዴም በግል በሚቀርብ ጥያቄ በፖሊሶች ይሁንታ ከሚፈቀድ ውጪ የመጸዳጃ ቤት እንዲሄዱ አይፈቀድላቸውም::

በጣም ጥቂት የፖሊስ ጣቢያዎች ደግሞ (ለምሳሌ ባሌ ሮቤ፣ ሻሸመኔ፣ አዳባ) እስረኞች ቀን ቀን በፈለጉ ጊዜ የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት እንዲያገኙ ይፈቅዳሉ:: በሌላ በኩል እስረኞች ሊያመልጡ ይችላሉ በሚል ስጋት ሁሉም የፖሊስ ጣቢያዎች ከመሸ በኋላ እስረኞች ከክፍላቸው ወጥተው መጸዳጃ ቤት እንዲሄዱ የማይፈቅዱ በመሆኑ ህመም የሚያጋጥማቸው እስረኞች ጭምር አገልግሎቱን ለማግኘት የሚቸገሩ መሆኑን እስረኞች ይገልጻሉ::

ከላይ ከተገለጸው በተለየ መልኩ ክትትሉ በተደረገበት ወቅት የጀልዱ ፖሊስ ጣቢያ የራሱ የመጸዳጃ ቤት ያልነበረው በመሆኑ እስረኞች ከፍተኛ የንጽህና ጉድለት ባለበት ሁኔታ በወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ ባለው ክፍት ቦታ ላይ የሚፀዳዱ መሆኑን የክትትል ቡድኑ ተመልክቷል:: ስለ ችግሩ የተጠየቁት የጣቢያው የምርመራ ክፍል ኃላፊ መጸዳጃ ቤት ለመገንባት በተደጋጋሚ የበጀት ጥያቄ ያቀረቡ ቢሆንም የተጠየቀው በጀት ባለመመደቡ ምክንያት እስረኞች በመጸዳጃ ቤት እጦት ለከፍተኛ ችግር መዳረጋቸውን ተናግረዋል:: ይሁንና የክትትል ቡድኑ በወቅቱ የሰጠውን ምክረ ሃሳብ ተከትሎ የፖሊስ ጣቢያው አስተዳደር ባደረገው ጥረት ጊዜያዊ የመጸዳጃ ቤት ማመቻቸት መቻሉን የፖሊስ ጣቢያው አስተዳደር ለኢሰመኮ መረጃ አድርሷል::

አብዛኞቹ የመጸዳጃ ቤቶች ከፍተኛ የንጽህና ጉድለት ይታይባቸዋል:: በአወዳይ ፖሊስ ጣቢያ ለተጠርጣሪዎች ተብሎ የተዘጋጀ አንድ የመጸዳጃ ቤት ብቻ ነው ያለው:: እሱም ቢሆን ሞልቶ

በጊዜ ባለመመጠጡ ምክንያት ለመጠቀም የማይቻል ከመሆኑም በላይ ወደ እስረኞች የመኖሪያ ክፍሎች እየፈሰሰ በአከባቢው መጥፎ ሽታ እና የበሽታ ስጋት ፈጥሯል፡፡

በአጠቃላይ ከመጸዳጃ ቤት አገልግሎት ጋር በተያያዘ በተነሱት ችግሮች ላይ ከየጣቢያዎቹ አመራሮች ጋር በነበረው ውይይት የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ወጥ የሆነ አሰራርም ሆነ መመሪያ አለመኖሩን እና ሁሉም ጣቢያዎች የየራሳቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተጠርጣሪዎች መጸዳጃ ቤት መጠቀም የሚችሉበትን ጊዜ ከሁለት እስከ ሦስት አድርገው የሚወስኑ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለዚህ ደግሞ በቂ የጥበቃ ሃይል ያለመኖር እና እስረኞች ሊያመልጡ ይችላሉ የሚል ስጋት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፡፡ እስረኞች በቀን ሁለት ጊዜ የመጸዳጃ አገልግሎት ካገኙ በቂ ነው የሚል አቋም ያንፀባረቁ አንዳንድ አመራሮችም ነበሩ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ለሚታዩ የመጸዳጃ ቤት እጦት እና የንጽህና ጉድለት ኃላፊዎቹ የበጀት እጥረትን በምክንያትነት ያነሳሉ፡፡

### 3.10. የሕግ ማዕቀፍ አለመኖር

ክትትሉ የተደረገባቸው ሁሉም ፖሊስ ጣቢያዎች የእስረኞችን አያያዝ በተመለከተ ግልጽ እና አስገዳጅ የሆነ መመሪያ የላቸውም፡፡ ለምሳሌ የቤተሰብ ጉብኝት፣ የመጸዳጃ ቤት አጠቃቀም፣ የማቆያ ክፍሎች ንጽህና፣ የክፍሎች ስፋት እና የእስረኞች ብዛት፣ የሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ፣ የእስረኞች አካላዊ ደህንነት እና የጣቢያዎቹ ኃላፊነት እንዲሁም እስረኞች በፖሊስ ጣቢያዎች መብታቸው ሲጣስ የውስጥ የቅሬታ አቀራረብን በሚመለከት የፖሊስ ጣቢያዎቹ ኃላፊዎች ተገቢ በመሰላቸው መንገድ ከሚወስኑት ውጪ ገዢ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ የሌላቸው መሆኑ በእስረኞች አያያዝ ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## 4. ምክረ-ሃሳቦች

ኢሰመኮ በዚህ ሪፖርት የተመለከተው የተወሰኑ ቦታዎችን ቢሆንም፤ ተመሳሳይ የሰብአዊ መብቶች ችግሮች በብዙ የክልሉ አከባቢዎች የሚስተዋሉ መሆኑን በተለያዩ ጊዜያት ለኮሚሽኑ ሲቀርቡ ከነበሩ አቤቱታዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሁሉም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የችግሮቹን አሳሳቢነት በመረዳት ከታች የተዘረዘሩትን ምክረ ሃሳቦች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ኢሰመኮ ጥሪ ያቀርባል፡፡

***ለኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን እና ለኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ***

- ☞ የፍርድ ቤት ውሳኔን በመጻረር በእስር ላይ እንዲቆዩ የተደረጉ እስረኞች በሙሉ በአስቸኳይ እንዲፈቱ፤
- ☞ በፀጥታ ኃይሎች ድብደባ እና ሌሎችም ኢሰብአዊ ድርጊቶች የተፈጸመባቸው እስረኞችን ጉዳይ በማጣራት ተጎጂዎች ፍትሕ እንዲያገኙ እና የሙያ ሥነምግባር ጉድለትና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን የፈጸሙ የፖሊስ አባላት ተጠያቂ እንዲሆኑ እንዲደረግ እና ለወደፊትም ተመመሳሳይ ድርጊቶች እንዳይደገሙ አስፈላጊ የሆነው የቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጋ፤
- ☞ የተጠረጠሩበት ወንጀል ሳይነገራቸው፣ ምርመራ ሳይደረግባቸው እና ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ለረጅም ጊዜ በእስር ላይ የሚገኙ "በወቅታዊ ሁኔታ" የታሰሩ የሚባሉ ተጠርጣሪዎች ምርመራቸው እንዲፋጠን እና ፍ/ቤት ቀርበው ፍትሃዊ ውሳኔ እንዲሰጣቸው እንዲደረግ፣ በወንጀል ሊያስከስሳቸው የሚያስችል ማስረጃ ያልተገኘባቸው ተጠርጣሪዎች እንዲለቀቁ፤
- ☞ በወንጀል የሚፈለግ የቤተሰብ አባል አቅርቡ ተብለው በእስር ላይ ያሉ ሰዎች በስቸኳይ እንዲፈቱ፤ እንዲሁም ወደፊትም ተመሳሳይ ድርጊቶች አንዳይደገሙ ግልጽ የሆነ አመራር እንዲሰጥ፤
- ☞ ከፍተኛ የእስረኛ መጨናነቅ ባለባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች የእስረኞችን ቁጥር ለመቀነስ የሚረዱ አፋጣኝ እርምጃዎች እንዲወሰዱ፤ እንዲሁም ተጨማሪ የማረፍያ ክፍሎች እንዲገነቡ፣ የንጽህና ሁኔታን ለማሻሻል አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ፣
- ☞ የፍትሐ ብሔር ግዴታዎችን ካለመወጣት ጋር በተያያዘ የታሰሩ ሰዎች በአስቸኳይ ከእስር እንዲፈቱ እና ለወደፊትም ተመሳሳይ ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ ግልጽ የሆነ አመራር እንዲሰጥ፣
- ☞ በማንኛውም ጊዜ ለሕጻናት እና ሴቶች ተጠርጣሪዎች ቅድሚያ ተሰጥቶ የተጠረጠሩበት ወንጀል በአፋጣኝ ምርመራ እንዲደረግ፤
- ☞ የሕጻናት ልጆች እናቶች በተቻለ መጠን በዋስ ተለቀው ጉዳያቸውን ከውጪ ሆነው መከታተል የሚችሉበት ሁኔታ እንዲመቻች፤
- ☞ በወንጀል ነክ ጉዳዮች ተሳታፊ ናቸው በሚል ተጠርጥረው የታሰሩ  እድሜያቸው ከ 9 እስከ 15 ዓመት የሚሆናቸው ሕጻናት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 172 መሰረት  በአፋጣኝ በዋስ እንዲለቀቁ፡፡

**ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳደር**

- ☞ በዞን እና በወረዳ ደረጃ የተቋቋሙ "የፀጥታ ምክር ቤቶች" የፍትሕ አካላትን ስልጣን እና ተግባር ባከበረ መልኩ እንዲሰሩ እንዲደረግና ከሰዎች መታሰርና ከእስር መለቀቅ ጋር በተያያዘ የሚያከናውኑትን ተግባሮች እንዲያቆሙ፤
- ☞ በተለያዩ ቦታዎች የሥራ ስምሪት የሚሰጣቸው የፀጥታ ሀይሎች ተገቢ የሆነ ቁጥጥር እንዲደረግባቸው፡፡

**ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለጨፌ ኦሮሚያ**

- ☞ በዚህ ሪፖርት የተገለጹ አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኙ የኮሚሽኑ ምክረ ሀሳቦች እየተፈጸሙ መሆኑን በቅርበት ክትትል እና ቁጥጥር እንዲደረግ፤ ኢሰመኮ ጥሪ ያደርጋል፡፡